በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

**የሰ/መ/ቁ.** 216561

ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** ወ/ሮ ማርታ ጎቤቦ፡- ጠበቃ መንክር ግርማ ቀርበዋል

**ተጠሪዎች-** 1. አቶ በቀለ አቤሮ፡- ተወካይ ታደሰ በቀለ ቀርበዋል

2. አቶ ዘለቀ ገ/ዮሐንስ፡- ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውል ይፍረስልኝ የዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት ሃዲያ ዞን የሴሞ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ እኔ እና 1ኛ ተጠሪ ባልና ሚስት ስንሆን የጋራ ንብረታችን የሆነውን በሸቻና ሮማ ቀበሌ በሰሜን መንገድ፣ በደቡብ በቀለ አቤሮና ተካሽ፣ በምስራቅ ወዕሎሮ አቤሮ እንዲሁም በምዕራብ መንገድ ከሚያዋስኑት 2.8 ሄክታር የእርሻ መሬት ውስጥ 1000 ካሬ ሜትር የሚሆነውን 1ኛ ተጠሪ በቀን ግንቦት 14 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ ውል በመሬቱ ላይ አራት ክፍል ቤት እንዳለው እና አመልካችም በሌለሁበት በውሉ ላይ እንደፈረምኩ በማስመሰል በብር 80,000.00 ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠለት በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ሚስቴ ስትሆን ሳላማክራት በቀን ግንቦት ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ ውል 530 ካ.ሜ መሬት በብር 80,000.00 ለ2ኛ ተጠሪ ሸጬለታለሁ፤ በዚህም ምክያት ትዳሬ እና ቤተሰቤ ሰላም በማጣቱ 2ኛ ተጠሪ ገንዘቡን እንዲወስድና መሬቱን እንዲመልስ ብጠይቀው ፍቃደኛ አልሆነም፤ ስለሆነም አመልካች በጠየቀችው መሠረት ህገ-ወጥ የሆነው የገጠር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሬት ሽያጭ ውል ፈርሶና 2ኛ ተጠሪ ገንዘቡን ወስዶ መሬቱን እንዲመልስ ቢወሰን ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ ግንቦት 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተደረገው የቤትና የቦታ ሽያጭ እንጂ የመሬት ሽያጭ ውል አይደለም፤ በውሉም ላይ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበት ሲሆን ቤቱን ከገዛሁ በኋላም ከፍተኛ ገንዘብና ጉልበት አውጥቼ በላሜራ ሱቅ እና ውሃ ልክ አሰርቼበታለሁ፤ አመልካች ሽያጩ የንብረት እንጂ የመሬት ባለመሆኑ ህገ-መንግስቱን የሚቃረን አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ 2ኛ ተጠሪ የገዙት በ530 ካ.ሜ መሬት ላይ ያረፈ አራት ክፍል ቤት እንጂ አመልካች እንደሚሉት 1000 ካ.ሜ የእርሻ መሬት አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡ በመቀጠል የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ህዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች በአከራካሪው ውል ላይ እንዳልፈረምኩ ክጄ ተከራክሬ እያለ ፍርድ ቤቱ በውሉ ላይ ያለውን ፊርማ በፎረንሲክ ሳያረጋግጥ ውሳኔ መስጠቱ፤ አከራካሪው ይዞታ የእርሻ መሬት መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ቦታው ድረስ በመሔድ አረጋግጦ እያለ ሽያጩ የቤት ነው በማለት 2ኛ ተጠሪ ያቀረበውን መከራከሪያ ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ተፈፀመ በተባለው የሽያጭ ውል ላይ አልፈረምኩም፣ ፍቃዴንም አልሰጠሁም እያሉ ባለበት ሁኔታ ይዞታው የገጠር ነው? ወይስ የከተማ? የሚለው ሳይጣራ ክሳቸው ውድቅ የተደረገበት አግባብ ከክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ እና ከቤተሰብ ህጉ ጋር ተገናዝቦ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ ጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው በሰጡት መልስ አመልካች ባቀረበችው አቤቱታ መሠረት ቢወሰን ተቃውሞ የለኝም በማለት የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበችው ክርክር በውሉ ላይ ያለመፈረሚን ሳይሆን ተሳስታ የፈረመች መሆኑን በመግለጽ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ተሳስታለች ወይስ አልተሳሳተችም የሚለውን አጣርቶ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ፊርማውን በፎረንሲክ ማስርመር አይጠበቅበትም፤ ውሉ የተደረገውም በገጠር ክልል ውስጥ በተሰራ ቤት ላይ እንጂ በእርሻ መሬት ላይ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታ ምክንያት በሆነዉ ዉሳኔ ላይ

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም የስር የክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱት በተጠሪዎች መካከል በተደረገዉ ዉል የተሸጠዉ በ530 ካ/ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ አራት ክፍል ቤት ስለመሆኑ መረጋገጡን እና በደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 2(6) አርሶ አደር በመሬት ላይ በጉልበቱ ያፈራዉን ንብረት መሸጥ እንደሚችል የደነገገ መሆኑን እንዲሁም አመልካች በዉሉ ላይ የፈረሙ ስለመሆኑ ተረጋግጧል የሚል ምክንያት በመስጠት ስለመሆኑ የዉኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ ፍርድ ቤቶች በዚህ መልኩ የሰጡትን ዉሳኔ በመቀበል የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ በትዕዛዝ ዉድቅ ማድረጉንም ተመልክተናል፡፡

እንደሚታወቀዉ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘዉ በክልሉ የሰማ ወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 12592 ጥቅምት 25 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም